Age-Friendly DC

# የዲሲ የአረጋውያን ምቹ ከተማ ተነሳሽነት

የዲሲ የአረጋውያን ምቹ ከተማ ተነሳሽነት በዓለም የጤና ድርጅት (WHO) ሁለት ጉልህ የሆኑ ማህበራዊ ሂደቶችን ማለትም በከተማ መስፋፋት እና የአረጋውያን ቁጥር መጨመር ምክንያት የተጀመረ የዓለም አቀፍ ጥረት አካል ነው። ከ2007 ዓ.ም. ጀምሮ ከግማሽ በላይ የሚሆነው የዓለም ህብረተሰብ የሚኖረው በከተማ ውስጥ ሲሆን በ2030 ዓ.ም. የዚህ ህዝብ ቁጥር ከእያንዳንዱ አምስት የዓለም ህዝብ ውስጥ ከተማ ይሚኖረው ወደ ሶስት ከፍ ይላል። በዚሁ ጊዜ ውስጥ የህብረተሰቡ የጤና መሻሻል ብዙ ሰዎች ረጅም ህይወት እንዲኖሩ አድርጓል። 60 እና ከዛም በላይ ዕድሜ ያለው የዓለም ህዝብ ብዛት መጠን በ2006 ዓ.ም. ከነበረው 11 በመቶ በ2050 ዓ.ም. በእጥፍ ወደ 22 በመቶ ሊጠጋ ይችላል። እነኝህን ሁለት ሂደቶች በተመለከተ ከተሞችን የበለጠ ለማዘጋጀት WHO የዓለም አቀፍ የአረጋውያን ምቹ ከተሞች ፕሮጀክትን ነድፏል። WHO በመላው ዓለም የሚገኙ የአረጋውያንን ጤንነት እና የኑሮ ምቾት የሚረዱ ስምንት ሰፋፊ ዘርፎች አሉት። የኮሎምቢያ ዲስትሪክት ሁለት ዘርፎች በመጨመር አስር ዘርፎች አሉት፣

1. ***የውጭ መዝናኛ ቦታዎች እና ህንፃዎች*** - ደህንነቱ የተጠበቀ የመዝናኛ ፋሲሊቲዎች መኖር እና ተደራሽ መሆን።
2. ***መጓጓዣ*** - ደህንነቱ የተጠበቀ እና በተመጣጣኝ ዋጋ የግል እና የህዝብ መመጓጓዣ ዘዴዎች።
3. ***የመኖሪያ ቤት*** - ለአረጋውያን የሚሆኑ ሰፊ የመኖሪያ ቤት አማራጮች፣ በመኖሪያ ቤታቸው የመቆየት እና ሌሎች የመኖሪያ ቤት ማሻሻያ ፕሮግራሞች።
4. ***ማህበራዊ ተሳትፎ*** - አረጋውያን በማህበራዊና ሲቪክ እንቅስቃሴዎች ከእኩዮቻቸው እና ከወጣቶች ጋር እንዲሳተፉ የባህላዊ እና የመዝናኛ ዕድሎች መፍጠር።
5. ***አክብሮት እና ማህበራዊ ተሳትፎ*** - የብዙ ትውልድ ውህደት እና ውይይቶችን ከሚያበረታቱ ፕሮግራሞች ጋር ባህላዊ እና የብሄር ውህደትን መደገፍ እና ማስፋፋት።
6. ***የህዝብ ግንኙነት እና ሥራ*** - ለአረጋውያን ነዋሪዎች የክፍያ ሥራ እና የበጎ ፈቃድ አገልግሎት እንቅስቃሴዎች መገፋፋት እና ከህይወታቸው ጋር በተያያዘ ፖሊሲዎች ላይ እንዲሳተፉ ዕድል መስጠት።
7. ***መገናኛ እና መረጃ*** - ቴክኖሎጂ በመጠቀም አረጋውያን ነዋሪዎች ከማህበረሰቡ እና ከጓደኞቻቸው እንዲሁም በቅርብ እና በሩቅ ከሚገኙ ቤተሰቦቻቸው ጋር እንዲገናኙ ጥረት ማድረግና ማበረታታት።
8. ***የህብረተሰብ ድጋፍ እና የጤና አገልግሎቶች*** - ጤናማ እና ንቁ አረጋዊነትን ለማበረታታት የቤት ውስጥ እንክብካቤ አገልግሎቶች፣ ክሊኒኮች እና ፕሮግራሞች እንዲኖሩ ማድረግ።
9. ***ለድንገተኛ አደጋ ምላሽ እና ዝግጁነት፣ የዲሲ ትኩረት*** - በአደጋ ጊዜ የአረጋውያንን ደህንነት፣ ጤና እና ዝግጁነትን ለማረጋገጥ መረጃ እና ሥልጠና መስጠት።
10. ***የአረጋውያን ጥቃት፣ ችልተኝነት እና ማጭበርበር፣ የዲሲ ትኩረት*** - የአዛውንቶችን ገንዘብ አላግባብ ማባከን፣ ችለተኝነትን፣ የአካላዊ፣ የፆታ እና ስሜታዊ ጥቃቶችን ማስወገድ እና መዳኘት።